የኢትዮጵያ የእንስሳት ሐኪሞች ማህበር

መተዳደሪያ ደንብ

ጥቅምት 2002
አዲስአበባ ኢትዮጵያ

BY LAW OF ETHIOPIAN

VETERINARY ASSOCIATION

OCTOBER 2009
ADDIS ABABA, ETHIOPIA

መግቢያ፡ - የኢትዮጵያ የእንስሳት ሐኪሞች ማህበር ከዚህ በታች በዝርዝር የተገለጹትን ዓላማዎች ለማሳካት በ*1968* ዓ.ም. የተቋቋመ አንጋፋ የሙያ ማህበር ነው፡፡

አንቀጽ 1፡ መቋቋም

የኢትዮጵያ የእንስሳት ሐኪሞች ማህበር የተባለ ማህበር በ 15 ቀን በ ሠኔ ወር በ *1968* ዓ.ም. ተቋቁሟል፡፡

አንቀጽ 2፡ ስያሜ

በዚህ መተዳደሪያ ደንብ የተቋቋመዉ ማህበር የኢትዮጵያ እንስሳት ሐኪሞች ማህበር በሚል ስም የሚጠራ ሲሆን ከዚህ በኋላ "**ማህበር**" ተብሎ ይጠቀሳል፡፡

አንቀጽ 3፡ ዓላማ

የማህበሩ አላማዎች የሚከተሉት ናቸዉ፤

ሀ) የማህበሩ አባላት በወቅታዊ የእንስሳት ሕክምና በተጓዳኝ የሰዎች ሕክምና ጥበብ እንዲሁም በስነ-ሕዮታዊ እና በግብርና ሙያ እንዲጐለብቱ ማድረግ ነው፡፡

ለ) ማህበሩ የእንስሳት ሕክምና እና ተጓዳኝ ሞያዎች የመረጃ መረብና ዋንኛ የመልእክት ማስተላለፊያ ማእከል በመሆን ያገለግለል፡፡ ለዚህ አላማው ማስፈጸሚያ የሚታተሙ የኢእሐማ ዝክረ መረጃ መጽሐፍ (EVA Journal) የጉባኤ ውጤቶች (Proceeding) እንዲሁም ዝክረ ዜናዎች (News Review) ያሳትማል፡፡ ለአባላቱና ለተጠቃሚ ድርጅቶች ያደርሳል፡፡

ሐ) ከመንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር በእንስሳት ጤና እና ምርትና ምርታማነት

Preamble: - The Ethiopian Veterinary Association is an indigenous association established in 1976 to meet the objectives mentioned herein below;

Article 1: Establishment

The Ethiopian Veterinary Association was established on June 22, 1976.

Article 2: Synonym

1. The association established in this article of association is The Ethiopian Veterinary Association herein after called "Association"

Article 3: Objectives

The objectives of the association are the following

A. To enable members develop their veterinary and human biological medicine and agricultural profession.
B. The association serves as a bridge for the veterinary medicine and other related professions networking platform. The journal printing for this purpose known as EVA Journal incorporates the proceedings and News Reviews and distribute to the members and beneficiaries.
C. Cooperate and operate closely with the concerned government bodies and play its own roles in the Conduct discussions and researches in collaboration with governmental and non governmental organizations.

ዙሪያ ውይይቶችና ጥናቶችን ያካሄዳል፡፡ ከሚፈለገው የመንግሥት አካል ጋር በቅርበት በመስራት ደንቦች መመሪያዎች እና የልማት አቅጣጫዎች የእንስሳትን ጤንነትና ደህንነት እንዲሁም ምርታማነትን ከማሻሻል አካያ እንዲቀረጽ ተጽእኖ ያሳድራል፡፡

መ) ባለሙያው ሙያዊ ስነምግባርን በተላበሰ እና የሞያውን ደረጃና ክብር በጠበቀ መልኩ ሙያውን እንዲገለገልበት ሙያዊ ደንቦችና መመሪያዎች እንዲወጡና በስራ ላይ እንዲውሉ ያደርግል፡፡

ሠ) ማህበሩ የእንስሶት ሕክምና እና ተጓዳኝ ሙያዊ ትምህርቶች ጥራትና ደረጃቸውን በጠበቀ መልኩ እንዲሰጡ ሙያዊ ድጋፍ ያደርጋል፡፡

ረ) ማህበሩ ሙያዊ የፈጠራ ነጻነት እንዲኖርና የፈጠራ ባለቤትነት እንዲከበር ይጥራል፡፡

ሰ) ባለሙያው በግል የእንስሳት ሕክምና ዘርፍ በመሠማራት ውጤታማ እንዲሆኑ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር በመተባበር ሞያዊ ክህሎትን ለማሳደግ ይጥራል፡፡

አንቀጽ 4፡ የበጀት ዓመት

የማህበሩ የበጀት ዓመት ከሐምሌ 1 እስከ ሰኔ 30 ይሆናል፡፡

አንቀጽ 5፡ ትርጉም

1. ‘‘ማህበር’’ ማለት በዚህ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት የተቋቋመዉ የኢትዮጵያ የእንስሳት ሐኪሞች ማህበር ነዉ፡፡
2. ኤጀንሲ ማለት በአዋጅ ቁጥር 621/2001 የተቋቋመዉ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ ነዉ፡፡

D. veterinary health sector thereby directing the rules and regulations of the development activities.

C. Ensure that the professional ethics and standard are respected and utilized complying with the rules and regulations.

D. The association supports the veterinary and related educational activities shall keep their quality and standards

E. The association strives for creativity and freedom of patent rights

H. Operates to develop the veterinary career thereby professionals develop their expertise and operate their own, governmental and non governmental organizations.

Article 4: Fiscal year

The fiscal year of the association is from July 1 to June 30 Ethiopian Calendar.

Article 5: Interpretations

1 “General assembly” means the highest authority of the association bearing founding members and other members in this article.

2 “Association” means The Ethiopian Veterinary Association established in this article of association.

3. ጠቅላላ ጉባኤ ማለት መስራች አባላትንና በዚህ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት ተቀባይነት ያገኙ ሌሎች አባላትን ያቀፈ የማህበሩ የበላይ አከል ነዉ።

አንቀጽ 6፡ አባላት፤

አንቀጽ 6.1፡ መደበኛ አባላት

1. መስራች አባላትንና በዚህ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት በጠቅላላዉ ጉባኤ ዉሣኔ ተቀባይነት ያገኙ አባላትን ይይዛል።
2. የሚከተሉትን መመዘኛዎች የሚያሟላ/የምታሟላ ማንኛ ዉም/ዋም ኢትዮጵያዊ/ት ሰዉ መደበኛ አባል መሆን ይችላል/ትችላለች።
   - ሀ) በእንስሳት ሕክምና ሙያ ትምህርት ስልጥኖ ትምህርቱን ያጠናቀቀና በሀገር ውስጥ በሙያው የተመዘገበ የእንስሳት ሕክምና ባለሙያ
   - ለ) በማህበሩ አላማና ግብ የሚያምን /የምታምን፤
   - ሐ) እድሜዉ/ዋ ከ20 ዓመት በላይ የሆነ/ች
   - መ) የማህበሩን የመተዳደሪያ ደንብ እንዲሁም በጠቅላላ ጉባኤዉ በየጊዜዉ የሚወጡ የስነምግባር ደንቦችን የሚቀበል / የምትቀበልና ተግባራዊ የሚያደርግ / የምታደርግ፤
   - ሠ) በአባላት ጠቅላላ ጉባኤ በየጊዜዉ ስምምነት የሚደረግባቸዉን ክፍያዎችና መዋጮዎች መክፍል የሚችል/የምትችል፤
   - ረ) በሕግ መብቱ/ቷ ያልተገፈፈ

አንቀጽ 6.2፡ ተባባሪ አባላት

ሀ) በትምህርት ልምምድ ላይ የሚገኝ ዕጩ የእንስሳት ሐኪም፣

3 “Agency” means an agency for associations established in accordance with proclamation number 621/2001.

Article 6: Membership

Article 6.1: Regular members

1. Including founding members and members admitted by the general assembly
2. Any Ethiopian fulfilling the following criteria will be taken as member

A. A locally registered veterinarian who has completed education
B. Accepting the association’s objectives and goals
C. Aged above 20 years
D. Complies with the article of association and the general assembly decisions
E. Able to pay contribution fees decided by the general assembly
F. Not legally prohibited

Article 6.2: Cooperative member

A. An apprentice and a veterinarian candidate

ለ) በሥራ አመራር ቦርድ የማህበሩን አላማ ለማሳካትና በእንስሳት ጤናና በእንስሳት ሀብት ልማት ዙሪያ ድጋፍ ሊሰጡ ይችላሉ ተብሎ የታመነባቸው የእንስሳት ጤናና ተጓዳኝ ሙያዎች ላይ የተሰማሩ ባለሙያዎች፣

ሐ) የማህበሩን ዓላማ የሚደግፉ ድርጅቶች የማህበሩ ተባባሪ አባላት ሊሆኑ ይችላሉ::

አንቀጽ 6.3: የሕይወት ዘመን አባል

ሀ) ማንኛውም የማህበሩ መደበኛ አባል የሃያ ዓመት የአባልነት ቅድሚያ ክፍያ በመክፈል የማህበሩ የሕይወት ዘመን አባል ለመሆን ይችላል::

ለ) የሕይወት ዘመን አባል የሆነ የማህበሩ አባል ዓመታዊ ክፍያ መክፈል የማይጠበቅበት ሲሆን የአባልነት መብቱና ግዴታውን ግን በሕይወት ዘመኑ ሁሉ ሊጠቀምበት ይችላል ::

አንቀጽ 6.4: የክብር አባላት

1. የማህበሩ አባል ያልሆኑና የማህበሩን ኣላማ ለማስፈጸም ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረከቱ ፤ ማህበሩ በሚሰራባቸዉ ዘርፎች ተሰማርተዉ ዉጤታማና የለዉጥ አርአያ በመሆን በማህበሩ አባላት ከፍተኛ ተቀባይነትን ያገኙ ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች በጠቅላላ ጉባኤዉ ዉሳኔ የክብር አባል
2. ይሆናሉ::የክብር አባላት በማህበሩ ዉስጥ የመምረጥ የመመረጥና ድምጽ የመስጠት መብት አይኖራቸዉም::
3. የክብር አባላት በራስ ተነሳሽነት ከልሆነ በቀር የአባልነት መዋጮችንና ሌሎች ክፍያዎችን የመክፈል ግደታ አይኖርባቸዉም::

B. Professionals who are operating the veterinary and related activities such activities approved by the management board to meet the objectives of the association.
C. The supporting organizations can be cooperating members

Article 6.3: Life time member

A. Any regular member of the association will be a life time member by advance payment of twenty years membership contribution fees.
B. A life time member is not expected to pay the annual contribution fees and can exercise in his/her life time the entitlements of the membership

Article 6.4: Honorary members

1. Those who contributed to the success of the association with out being member and those who are engaged similar with the association becoming role models in succeeding in good performances and become members in accordance with the decisions of the general assembly.
2. The honorary members have no right to vote and to be contenders.
3. Unless with self motion, they are not obliged to pay for the contribution and other fees.

አንቀጽ 7፡ የአባልነት መመዘኛ

ማንኛውም አባል የሚከተሉትን ማሟላት አለበት፡-

ሀ) የአባልነት ቅጽ መሙላት፣

ለ) ተገቢውን የአባልነት ክፍያ መክፈል፣

ሐ) የማህበሩን መተደደሪያ ደንብ ማክበር፣

መ) በማህበሩ የሥራ አመራር ቦርድ የአባልነት ጥያቄው ተቀባይነት ማግኘትና በጠቅላላ ጉባዔው መጽደቅ ይኖርበታል።

አንቀጽ 8፡ የአባላት መብት

1. ሁለም መደበኛ አባላት እኩል መብት አላቸዉ።
2. የማህበር አባልነት ለወራሾችም ሆነ ለሌላ ሰዉ የማይተላለፍ የግል መብት ነዉ።
3. ማንኛዉም የማህበሩ መደበኛ አባል
   - ሀ) ለማህበሩ ዓላማና ተልእኮዎች መሳከት የሚጠቅሙ ማናቸዉንም አይነት ስራዎች የመስራት
   - ለ) የመምረጥ፤የመመረጥና ስለማህበሩ እንቅስቃሴ ማንኛዉንም መረጃ ጠይቆ የማግኘት እና
   - ሐ) በጠቅላላዉ ጉባኤዉ ስብሰባ የመገኘት፤ ስለማህበሩ እንቅስቃሴ አስተያየትና ድምጽ የመስጠት መብት አለዉ / አላት።
   - መ) ማንኛዉም የማህበሩ መደበኛ አባል አባልነቱ እንዲቋረጥ የመጨረሻ ዉሳኔ ከመስጠቱ በፊት በስራ አስፈጻሚ ቦርድ የመስማት መብት አለዉ።
   - ሠ) ማህበሩ የሚሰጠውን ማናቸውም ጥቅምና መብት የማግኘት፣
   - ረ) ለማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ ተገዥ የመሆንና የሙያውን ሥነ ምግባር የማክበር፣

Article 7: Membership Requirements

Every member must fulfill the followings;

A. Filling the membership form
B. Pay membership fee
C. Respect the by laws of the association
D. The membership application shall be accepted by the board and approved by the general assembly of the association

Article 8: Rights of members

1. All regular members have equal rights
2. Membership is private and cannot be transferred to heirs
3. any regular member of the association has right to
   - A. Carry out any activities complying to the objectives and missions of the association
   - B. Vote, voted and get any information about the association on request
   - C. Participate in the general assembly meetings and comment on the operations of the association and to vote
   - D. Any member before decision of termination from the association has right to consult the executive board
   - E. The right to get all the benefits and rights from the association
   - F. Shall comply with the by laws of the association and respect the professional ethics

አንቀጽ 9፡ የአባላት ግደታ

1. ማንኛዉም/ዋም አባል የአባልነት መዋጮን በወቅቱ መክፈል አለበት፤
2. አንድ አባል ከአባልነት ከመሰናበቱ/ቷ በፊት የሚፈለግበትን/ የሚፈለግባትን ዕዳ መክፈል ይኖርባታል/ይኖርበታል፤
3. ማንኛዉም/ዋም አባል የማህበሩን የመተዳደሪያ ደንብ በጠቅላላ ጉባዔ የሚወጡ መመሪያዎችና ዉሣኔዎችን ማክበር አለበት/አለባት፤
4. ማንኛዉም/ዋም አባል የማህበሩን አላማና የገባቸዉን /የገባችዉን ግዴታዎች ማክበር፤ የማህበሩን ንብረት የመንከባከብና የሚጠቀምበትን አገልግሎት የመስጠት ግደታ አለበት/አለባት፤
5. በማህበሩ መደበኛ ና አስቸኩዋይ ስብሰባዎች ላይ የመገገኘት ግዴታ አለበት/አለባት፤

አንቀጽ 10፡ የአባላት መዋጮና ሌሎች ክፍያዎች

1. የማህበሩ መዋጮና ሌሎች ክፍያዎች የሚደረጉበት ጊዜና መጠን በጠቅላላ ጉባኤዉ እንዳስፈላጊነቱ እየታየ የሚወሰን ይሆናል፤
   ይህ መተዳደሪያ በፀደቀበት ወቅት የተወሰነዉ የአባልነት ክፍያ እንደሚከተለዉ ተወስኗል፡
   ሀ) መደበኛ አባላት ብር 120.00 በዓመት ይከፍላሉ፣
   ለ) ተባባሪ አባላት ብር 100.00 በዓመት ይከፍላሉ፣ነገር ግን ድርጅቶች ከሆኑ ብር 2,000.00 የአባልነት መዋጮ በዓመት ይከፍላሉ፡፡
   ሐ) የክብር አባላት የአባልነት ክፍያ አይከፍሉም፡፡
2. በጠቅላላ ጉባኤዉ በሚወሰነዉ የጊዜ ገደብ የማይከፍል/የማትከፍል ሰዉ በጠቅላላ ጉባኤዉ ዉሳኔ መሰረት መቀጮ ይጣልበታል/ይጣልባትል፤

Article 9: Obligations of members

1. Any member shall pay contribution fees on time
2. Before terminating membership, any member should clear all debts due to him/her
3. Any member must comply with the associations' article of association and directives of the general assembly
4. Any member must respect the objectives and obligations of the association and take care of the properties of the association, and render services expected of him/her
5. Any member must participate in regular and emergency meetings of the association

Article 10: Contribution fees and other payments

1. The time of and amount of contribution fee payment will be decided by the general assembly. The membership contribution decided during the approval of this article of association is as follows;
   A. Regular members pay Birr 120.00 annually
   B. The cooperative members pay Birr 100.00 annually but if they are organizations, the annual membership fee is Birr 2000.00 per year
   C. The honorary members will not pay membership fee
2. Any one failing to pay the contribution fees on time decided by the general assembly will be subject to charges by the general assembly.

3. የአባልነት መዋጮ ባለመክፈሉ/ሏ ምክንያት በጠቅላላ ጉባኤዉ የተጣለባትን ቅጣት የልከፈለ/ች አባል ላይ እዳዉን/እዳዋን እስኪከፍል/እስክትከፍል ድረስ ጠቅላላ ጉባኤዉ ድምጽ የመስጠት ወይም ማንኛዉንም ሌላ መብት ሊያነሳ ይችላል።

አንቀጽ 11፡ አባልነት ስለሚቋረጥባቸዉ ሁኔታዎች

አንድ የማህበሩ አባል አባልነቱ/ቷ የሚቋረጠዉ፡-

1. ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ/ስትለይ፤
2. መተዳደሪያ ደንቡ ላይ በተገለጸዉ መሠረት ወይም በሌላ አጥጋቢ ምክንያት ከአባልነት እንዲሰናበት/እንድትሰናበት ጠቅላላ ጉባኤዉ ሲወሰን፤
3. የማህበሩን ክብርና ህልዉና በሚነክ ወይም በሚያናጋ ተግባር ላይ መሳተፉ/ፏ በማስረጃ ሲረጋገጥና ይህም በጠቅላላ ጉባኤዉ ሲወሰን፤
4. ለማህበሩ ዓላማ መሳከት በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ዉስጥ ተገቢዉን ተሣትፎ ለማድረግ ፈቃደኛ ሳይሆን/ሳትሆን ሲቀር/ስትቀር እና ይኸዉ በጠቅላላ ጉባኤዉ ሲወሰን፤
5. መዋጮዉን ለአንድ አመት ያህል ጊዜ ባለመክፈሉ/ሏ በጠቅላላ ጉባኤዉ ከአባልነቱ/ቷ ሲሰናበት/ስትሰናበት፤
6. ስልጣን ባለዉ ፍርድ ቤት ችሎታዉን/ዋን ወይም መብቱን/ዋን ሲነጠቅ/ስትነጠቅ ወይም ከአባልነት ሲወገድ/ስትወገድ፤
7. ከማህበሩ አባልነት በራሱ/ሷ ፈቃድ ለመልቀቅ በጽሁፍ ሲጠየቅ/ስትጠይቅ ይሆናል፤

3. A member who failed to pay contribution fee on time and proceeding charges of the general assembly may be suspended from any right of voting until such payment is solved.


Article 11: Termination of membership

A member will be terminated

1. Due to death
2. When decided to be terminated by the general assembly of not complying with the articles of association
3. If found by evidences of violating the respect and honor of the association and decision of the general assembly
4. Failing to participate in activities of the association and when assembly decided by the general
5. Failure to pay contribution fees for the period of one year and thereof terminated by the general assembly.
6. When prohibited of ability by the authorized court and termination from membership
7. Written request from self to terminate from the welfare association


አንቀጽ 12፡ የማህበሩ አደረጃጀት

1. የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ፡ የስራ አመራር ቦርድ፡ ሥራ አስኪያጅ፡ አዲተር፡ ሂሳብ ሹም፡ ገንዘብ ያዥና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞች ይኖረዋል፤
2. ማህበሩ በሚከተለዉ መልኩ የተዋቀረ ነዉ፤
3. የቦርድ አባል የሆነ ማናቸዉም ሰዉ በተጨማሪ አዲተር ወይም ሥራ አስኪያጅ ሆኖ ሊሰራ አይችልም።



Article 12: Structure of the association

1. The association will have general assembly, executive board, general manager, auditor, treasurer, finance clerk and other necessary staffs
2. The association has the following structure (below)
3. Any board member cannot be an auditor or general manager.



አንቀጽ 13፡ የጠቅላላ ጉባኤው ስልጣንና ተግባር

1 ጠቅላላ ጉባኤው በዚህ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 5 ላይ የተጠቀሱትን መደበኛ አባላት የሚያካትት ሆኖ በህግና በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ) ጠቅላላ ጉባኤው የማህበሩ የበላይ አካል ነው፣

ለ) የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ ያወጣል፣ ያሻሽላል፣

ሐ) በመተዳደሪ ደንቡ መሠረት የማህበሩን ኦዲተር ይመርጣል፣ ያሰናብታል፣ ክፍያውን ይወስናል፣

መ) የቦርድ አባላትን፣ የጉባኤውን ሰብሳቢ፣ ምክትል ሰብሳቢ እና ፀሐፊ ይሾማል ይሽራል፣

ሠ) የማህበሩን ዋና መሥሪያ ቤት የመለወጥና ቅርንጫፎች የመክፈት የመጨረሻ ውሳኔ ያሳልፋል፣

ረ) ማህበሩን መፍረስና ንብረት ማጣራት ላይ ይወስናል፣

ሰ) የማህበሩን ዓመታዊ የሥራ ክንውን ሪፖርት፣ የሂሳብ መግለጫ፣ የኦዲት ሪፖርትና ዓመታዊ በጀት ያፀድቃል፣

ሸ) ዓመታዊ የሥራ ፕሮግራምን በመመርመር እቅድና በጀት ያፀድቃል፣

ቀ) በማህበሩ የፖሊሲና የስትራቴጂ ጉዳዮች ላይ ይወስናል፣

ሸ. የማህበሩ አባል ለመሆን በቀረበው ጥያቄ ላይ ውሳኔ ይሰጣ ል፣

ተ) በዚህ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 9 በተገለፀው መሠረት ግዴታውን ያልተወጣ አባልን ጉዳይ መርምሮ ከአባልነት እንዲሰረዝ ይወስናል፣

ቸ) የአባላት መዋጮ ሌሎች ክፍያዎችንና የቅጣት መጠን ላይ ይወስናል፣

የማህበሩ ሂሳብ በውጭ ኦዲተር እንዲመረመር ያደርጋል፣

ነ) የጠቅላላ ጉባኤውን የስብሰባ ሥነ-ስርዓት ደንብ ያወጣል፣

Article 13: Duties and Powers of the general assembly

1. The general assembly includes the following regular members mentioned in the article of association article 5 and has the following duties and powers:
   a) The general assembly is the highest authority of the association
   b) Designs the article of association and amends the same
   c) Appoint the auditor or dismiss and decide payments in accordance with the article of association
   d) Appoint or dismiss the board members, chairman of the assembly, deputy chairman and secretary of the general assembly
   e) Decides on the change of the headquarters of the association, opening branch offices
   f) Decides on dissolving and inventory of the association
   g) Approves the annual performance report, accounting and annual audit reports
   h) Evaluates the annual work programs and approve plan and budget
   i) Decides on policies and strategies of the association
   j) Decides on application of membership
   k) In accordance with the provisions of article 10, assess the case of member failing to comply with
   l) obligations and decides on cancellation of membership
   m) Decides amount of charges of punishment
   n) Enables external auditing of the accounts of the association
   o) Designs ethics of the meeting of the general assembly

ኘ) ማህበሩ ከሌሎች ማህበራት ጋር ህብረት ለመፍጠር ወይም ለመዋሃድ ወይም የመክፈል ወይም የመለወጥ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

አ) በማህበሩ ሌሎች አካላት ስልጣንና ተግባራት ስር በማይወድቁ ማህበሩን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ

2 ጠቅላላ ጉባኤው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ 1(ሠ)፣ (በ)፣ (ቸ) እና (ነ) መሠረት የተሰጡትን ስልጣንና ተግባራት ለማህበሩ አመራር አካላት ወይም ለሚያቋቁሙው ቋሚ ወይም ጊዜያዊ ኮሚቴ በውክልና ማስተላለፍ ይችላል፡፡

3. ጠቅላላ ጉባኤው ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ህግጋት ጋር ግጭት ከሌለው በስተቀር በዚህ መተዳደሪያ ደንብ ትርጉም ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

ይወስናል፡፡

አንቀጽ 14፡ የጠቅላላ ጉባኤ ድምፅ አሰጣጥ

1. ማንኛውም አባል በጠቅላላ ጉባኤው ስብሰባ ላይ ተገኝቶ/ታ ድምፅ በሚሰጥበት ጉዳይ ላይ የሚሰጠው/የምትሰጠው ድምፅ አንድ ብቻ ይሆናል፡፡
2. ማንኛውም የማህበር አባላት እኩል ድምፅ አላቸው፡፡
3. ጠቅላላ ጉባኤው በግልጽ ካልፈቀደ በስተቀር ማንኛውም አባል በስብሰባ ላይ እራሱ/ሷ ተገኝቶ/ታ ድምጽ መስጠት ይኖርበታል/ይኖርባታል፡፡
4. የድምጽአሰጣጡ ሥነ-ስርዓት ፍታሃዊ ነፃና ግልጽ በሆነ መንገድ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡
5. ከጠቅላላው ጉባኤ የተለየ ሃሳብ ያለው/ያላት የማህበር አባል የልዩነት ሃሳቡን/ቧን በቃል ገባጼው ላይ ለይቶ ማስፈር ይችላል/ትችላለች፡፡
6. ማንኛውም መደበኛ የማህበር አባል በጠቅላላ ጉባኤው የተላለፈው ውሣኔ የሃገሪቱን ህግጋት ወይም የማህበሩን

p) Decides on to cooperate with other associations or merge or pay or transfer

q) Decides on affairs of other duties and activities pertaining to the association

2. When necessary, the general assembly can transfer the duties and powers of the leadership of the association in accordance with this article 1(E), J, L and M for leaders or temporary committee.

3. Unless contradicts with pertinent laws, the general assembly gives final decision on interpretation of this article of association.

Article 14: Voting on general assembly

1. Any member has only one vote on the meetings of the general assembly
2. All members have equal vote
3. unless it is clearly permitted by the general assembly, any member shall be present on meetings to vote
4. the voting procedure shall be loyal, free and transparent
5. a member having different understanding to that of the general assembly can forward his/her understanding on the minutes of the meeting
6. Any regular member of the association when finding that decision of the general assembly violates the law of the country or article of association can apply to the agency.

መተዳደሪያ ደንብ ይጥሳል ብሎ/ላ ሲያምን/ስታምን ለኤጀንሲው ሊያመለክት/ልታመለክት ይችላል/ትችላለች።

አንቀጽ 15፡ የጠቅላላ ጉባኤው አመራር አካላት ሥልጣንና ተግባራት

ጠቅላላ ጉባዔው ፕሬዚዳንት፣ ምክትል ፕሬዚዳንት እና ፀሐፊ የሚኖረው ሲሆን ሥልጣንና ተግባራቸውም የሚከተለው ነው፣

1. ፕሬዚዳንት፣

ሀ. የጠቅላላ ጉባኤውን ስብሰባዎች ይጠራል/ትጠራለች ከፀሐፊው/ዋ ጋር በመሆን አጀንዳዎችን ያዘጋጃል/ታዘጋጃለች፣

ለ. የጉባዔውን ስብሰባ በሊቀመንበርነት ይመራል/ትመራለች፣

ሐ. ጠቅላላ ጉባኤው የሚያወጣቸውን ደንቦችና የሚሰጣቸውን ውሣኔዎች በትክክል ሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል/ትከታተላለች፣

መ. ጉባኤው ያጸደቃቸው ዓመታዊ የሥራ ክንውን፤ የሥራና የአዲት ሪፖርቶችና የሂሳብ መግለጫ ለሚመለከታቸው መንግሥታዊ አካላት እና እንደአስፈላጊነቱ ለተጠቃሚዎችና ለለጋሾች እንዲደርሱ ያደርጋል/ታደርጋለች፣

ሠ. ለጉባዔው የሚቀርቡ ጉዳዮችን ቅደም ተከተል በማውጣት ለውይይት እንዲቀርቡ ለፀሐፊው በአጀንዳነት ያስይዛል፣

2. ምክትል ፕሬዚዳንት፣

ሀ. ሰብሳቢው/ዋ በማይኖርበት/በማትኖርበት ጊዜ ተክቶ/ታ ይሠራል/ትሰራለች፣

ለ. በሰብሳቢው ወይም በጠቅላላ ጉባኤዉ የሚሰጡትን ሌሎች ሥራዎች ያከናውናል/ ታከናውናለች፣

Article 15: Duties and powers of the leadership of the general assembly

The general assembly has the president, deputy president and secretary who have the following duties and responsibilities

1. President of the general assembly

A. Calls meetings of the general assembly and prepares agenda of the meetings with the secretary
B. Leads the meeting of the general assembly as chairman
C. Monitors whether the directives and regulations of the general assembly are implemented
D. Enables reporting of the performances, performance and audit reports and accounting documents to the concerned government
E. authorities, beneficiaries and donors and government bodies
F. Prepares the procedures of the affairs of the assembly and inform the same to the secretary to keep agenda

2. Deputy president

A. Work in place of the president when the chairman is absent
B. Carry out other activities assigned by the general assembly

3. ፀሐፊ

ሀ. ከሰብሳቢው ጋር በመሆን ለጉባኤው አጀንዳዎችን ያዘጋጃል/ታዘጋጃለች፣

ለ. የጉባኤውን ስብሰባ ቃለ ጉባኤ ይይዛል/ትይዛለች፣

ሐ) ፕሬዚዳንቱና ምክትል ፕሬዚዳንቱ በሥራ መደባቸው ሳይገኙ ሲቀሩና ጠቅላላ ጉባዔው ተተኪ እስኪመረጥ ድረስ ተወካይ ተጠሪ ሆኖ ይሠራል።

<u>አንቀጽ 16፡ የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ</u>

1. የጠቅላላ ጉባኤው መደበኛ ስብሰባ ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ በጠቅላላ ጉባኤው ፕሬዚዳንት ጠሪነት የሚካሄድ ሆኖ የበጀት ዓመቱ ከተዘጋ በኋላ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ መካሄድ ይኖርበታል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ1 መሰረት ፕሬዚዳንቱ በ30 ቀናት ውስጥ ስብሰባ ያልጠራ እንደሆነ ኤጀንሲው በአንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ አባላት ጠያቂነት በ ፕሬዚዳንቱ አማካኝነት ወይም በራሱ የጠቅላላ ጉባኤውን ስብሰባ ሊጠራ ይችላል።

3. የጠቅላላ ጉባኤው ስብሰባ የተጠራው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ከሆነ ኤጀንሲው የጠቅላላ ጉባኤ ፕሬዚዳንት የሚሆን/የምትሆን ሰው ለምርጫ ሊያቀርብ ይችላል።

4. የማህበሩ አስቸኳይ ስብሰባ በማናቸውም ጊዜ በቦርዱ ፕሬዚዳንት ወይም ከማህበሩ 10 ከመቶ የሚሆኑት በሚጠይቁበት ጊዜ ሊካሄድ ይችላል።

5. ለጠቅላላ ጉባኤው መደበኛ ስብሰባ አስራ አምስት የሥራ ቀናት ለአስቸኳይ ስብሰባ ደግሞ ከአምስት የስራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ በፊት አባላት የስብሰባው ዝርዝር ጉዳይ፣ ቦታውን፣ ቀኑን፤ እንዲያውቁት ይደረጋል።

3. Secretary

A. Prepares agenda of the meetings with the president
B. Recording of the minutes of the meetings

<u>Article 16: Meetings of the general assembly</u>

1. The regular meeting of the general assembly will be conducted at least once every year with in 90 days of closing the fiscal year by call of the chairman
2. In accordance with this article sub article 1, if the chairman doesn't call the meeting within 30 days, the agency will by the request of one or more members through the chairman or self can call the meeting of the general assembly.
3. If the meeting is called as per this article sub article 2, the agency can appoint the chairman of the meeting
4. The emergency meeting of the association will be called at any time by the chairman of the board or 25% request of the members.
5. The call of the meeting shall be 15 days advance for regular meetings and 5 work days for emergency meetings mentioning agenda of the meeting, place, date and known to members

6. የማህበሩ አባላት ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፡፡
7. በዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 6 የተደነገገው እንዳለ ሆኖ ምልዓተ ጉባኤው ለሁለት ተከታታይ ስብሰባዎች ካልተሟላ የጠቅላላ ጉባኤው ሰብሳቢ የሚቀጥለው ስብሰባ በተገኙት አባላት እንዲካሄድ ያደርጋል/ታደርደጋለች፡፡
8. በጠቅላላ ጉባኤው መደበኛ ስብሰባ ላይ የተለያዩ ጉዳዮች እንደየሁኔታው በአጀንዳነት ተይዘው ለውይይት ይቀርባሉ፣ ማንኛውም ጉዳይ በአጀንዳ እንዲያዝለት የሚፈልግ አባል ጠቅላላ ጉባኤ ከመሰብሰቡ ቢያንስ ከአንድ ሳምንት በፊት ለጉባኤው ፀሐፊ / ፕሬዝዳንት / የጠቅላላ ጉባኤ ሰብሳቢ በጽሁፍ ይህንኑ ማስታወቅ ይኖርበታል / ይኖርባታል፡፡

አንቀጽ 17፡ የምርጫና የውሣኔ አሰጣጥ ሥነ-ስርዓት

1. ማህበሩ የሚመራው በአባላት ሙሉ ተሳትፎ በተመረጡ ሰዎች ይሆናል፣
2. ጉባኤው ምርጫ ሲያደርግ ምልዓተ ጉባኤው እንደተሟላ የአስመራጭ ኮሚቴ አባላት ተመርጠው ምርጫው እንዲያካሄድ ያደርጋሉ፣
3. አስመራጭ ኮሚቴው ከሁሉ አስቀድሞ የምርጫ መመዘኛዎች በጉባኤው እንዲወሰኑ አድርጎ ምርጫውን ያስፈጽማል፣
4. ጠቅላላ ጉባዔው የአገልግሎት ዘመናቸውን ያጠናቀቁ ወይም የተሻሩ ወይም በተለያዩ ምክንያቶች የተጓደሉ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላትን ለመተካት እንደአስፈላጊነቱ የስራ አመራር ቦርድ ኮሚቴ አባላትን ለመተካት እንደአስፈላጊነቱ የአስመራጭ ኮሚቴ ያቋቁማል፣
5. የምርጫ ዘመናቸውን ያጠናቀቁ ተመራጮች በድጋሚ እንዲያገለግሉ ከተፈለገ በጥቆማ ለውድድር ቀርበው በድምጽ

6. It is full quorum if more than 50% members are available
7. Notwithstanding to the premises of sub article 6, if the quorum is not fulfilled in two meetings, the chairman of the general assembly will conduct the next meeting.
8. On the regular meetings, different affairs will be put as agenda and discussed up on any one in need of agenda shall notify the secretary/chairman/president/general assembly chairman/ in writing in advance of at least one week.

Article 17: Voting and Decision making

1. The association will be led by the persons voted by members consent
2. when the assembly conducts voting, when the quorum is filled, the voting committee will be established and election will proceed
3. the election committee will enable criteria of election to be approved by the assembly and conduct election
4. Those who completed the service in the general assembly or dismissed or executive committee unfulfilled committee member replacement needs establishment of election committee
5. The finishing their service years when needed to serve again will be selected as candidates and elected by higher vote. But for the third term election, at least gap of 5 years is needed.

ብልጫ መመረጥ ይኖርባቸዋል፣ሆኖም ለ3ኛ ጊዜ ለመመረጥ ቢያንስ ለአንድ የምርጫ ዘመን/4 ዓመት/ማረፍ ይኖርባቸዋል።

6. የጠቅላላ ግባኤው ውሳኔዎች በድምፅ ብልጫ ያልፋሉ፣ ድምፅ እኩል ሲሆን ሊቀመንበሩ ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል፣
7. የማህበሩ የስብሰባ ሥነ-ስርዓት በማናቸውም ጊዜ ቢሆን የዲሞክራሲ መርሆችን የተከተለ መሆን አለበት፣
8. የአስመራጭ ኮሚቴ አባላት እራሳቸውን ለኮሚቴ ምርጫ በዕጩነት ማቅረብ አይችሉም። ሆኖም ግን የጠቅላላ ጉባኤው ካመነበት ከአስመራጭ ኮሚቴነት በማንሳት በእጩነት ሊያቀርባቸው ይችላል፣
9. አስመራጭ ኮሚቴው አዲሶቹ ተመራጮች 30 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ሥራቸውን ተረክበው እንዲሰሩ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፣
10. የቀድሞ ተመራጮች በምርጫ ከተሰናበቱ ዕለት ጀምሮ ከጠቅላላ ጉባኤ ውሣኔ ወጪ ከርክክብ በስተቀር ሥራውን ማንቀሳቀስ አይችሉም፣
11. በጠቅላላ ጉባኤው አጀንዳ ላይ ቀርበው ያልጸደቁና ያልሰፈሩ ጉዳዮችን በተመለከተ የተሰጡ ውሣኔዎች ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፣

አንቀጽ 18፡ የሥራ አመራር ቦርድ ሥልጣንና ተግባር

የሥራ አመራር ቦርድ ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባኤው ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የማኅበሩን ሥራ አስኪያጅ ይሾማል፣ ይሽራል፣
2. በጠቅላላ ጉባኤ የሚሰጡ ውሳኔዎችንና የሚወጡ እቅዶችን በሥራ አስኪያጁ ተግባራዊ መደረጋቸውን ይቆጣጠራል፣ ይከታተላል፣
3. የማህበሩን ፖሊሲ ለማውጣት ወይም ለማሻሻል የማህበሩ ሥራ አስፈፃሚ አካል የሚያቀርባቸውን ሀሳቦች ተቀብሎና አስፈላጊም

6. Decisions of the general assembly will be passed by high vote when votes are equal, the chairman will decide
7. Whenever there is the meeting of the assembly, shall be democratic
8. The members of election committee will not be candidates. But if the general assembly permits, shall be removed from member of committee and and assigned as candidates.
9. The election committee is obliged to make the election committee members to start service with in 30 days.
10. From the date of dismissal of existing members, they cannot do other activity other than handing over.
11. Cases not approved by the agenda of the general assembly are not enforced.

Article 18: Duties and powers of the management board

The management board accountable to the general assembly has the following duties and powers

1. Appoint or dismiss the manager of the association
2. Monitors and evaluates the implementation of the directives of the general assembly to be carried out by the manager
3. Accept the comments of the executive bodies of the association to set the policies or amend the same and by addition of self comment to be decided by the general assembly

ሲሆን የራሱን አስተያየት ጨምሮ ውሳኔ እንዲሰጥባቸው ለጉባኤው ያቀርባል፣

4. በገንዘብ ወይም በማቴርያል ለማህበሩ ፕሮግራም ማስፈጸሚያ የሚሆኑ ገቢዎች መኖራቸውን የረጋግጣል፣ ድጋፍ የሚገኝበትንም መንገድ ይቀይሳል፣
5. ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች አስፈላጊ በመሆኑ አካባቢዎች እንዳስፈጊነቱ ለጠቅላላ ጉባኤ አቅርቦ ያስወስናል፣
6. የማህበሩ የሥራ አስፈፃሚ አካላት የሚቀርቡ የሥራ አፈፃፀም ሪፖርቶችን መርምሮ ከአስተያየት ጋር ለጠቅላላ ጉባኤ ያቀርባል፣
7. ሠራተኞች የሚቀጠሩበትንና የሚተዳደሩበትን ደንብ ያወጣል፣
8. በማህበሩ የአጭር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ ዕቅድና በጀት ላይ በመምከር ለጠቅላላው ጉባኤ ለውሳኔ ያቀርባል፣
9. የሠራተኞች መተዳደሪያ ደንብ ያወጣል፣
10. የቦርዱን የስብሰባ ሥነ-ስርዓት ደንብ ያወጣል፣
11. አስቸኳይ የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ የሚጠራበት ምክንያት ሲያጋጥም ጥሪ እንዲደረግ ይወሰናል።

<u>አንቀጽ 19፡ የሥራ አመራር ቦርድ አባላት</u>

የሥራ አመራር ቦርድ ሰባት አባላት ይኖሩታል።

- ፕሬዚዳንት
- ምክትል ፕሬዚዳንት
- ፀሐፊ
- አራት አባላት

1. የሥራ አመራር ቦርድ 7 አባላት ይኖሩታል፣ (ቢሆንም የቦርዱ ቁጥር ውሳኔ አሰጣጥ እንዲያመች ጎዶሎ መሆን ይኖርበታል)

4. Approves income to the association in kind or cash and looks for ways to generate revenues
5. Decides the need to open branch offices after consenting from the general assembly
6. Assessment of the performance reports of the associations executive bodies and present to the general assembly with self comment
7. Sets directives to employ or dismiss employees
8. Discussing on the association's short, medium and long term plan and budget and present for the decision of the general assembly
9. Set the employees' administration directive
10. Sets directives of the board meetings
11. When ever there is necessity to call emergency meeting, decides to call of the meeting.

Article 19: Members of the management board

The management board has seven members

- President
- Deputy president
- Secretary
- Four other members

1. The management board has 7 members (must be odd number for passing decisions)
2. The manager will serve as board secretary with out right to vote

2. የማህበሩ ሥራ አስኪያጅ ድምጽ የመስጠት መብት ሳይኖረው የቦርዱ ፀሐፊ ሆኖ
ይሰራል::

3. ፕሬዚዳንቱ/ቷ፣

ሀ. የቦርዱን ስብሰባ በሊቀመንበርነት ይመራል/ትመራለች፣
ለ) ቦርዱ በስብሰባ ያሳለፋቸውን ውሣኔዎች ለጠቅላላው ጉባኤ ያቀርባል/ታቀርባለች፣
ሐ. ቦርዱ የሚያወጣቸውን የማህበሩን ፖሊሲዎች ፣ ስትራቴጂዎችና መመሪያዎች ለጠቅላላ ጉባኤው አቅርቦ/ባ የጸድቃል/ታጸድቃለች፣
መ. ለጠቅላላ ጉባኤውና ለቦርዱ ከተሰጠው ስልጣን አንፃር ተጠሪነቱ/ቷ ለጉባኤውና ለቦርዱ ይሆናል፣
ሠ. ጠቅላላ ጉባኤውና ቦርዱ በሚያሳልፏቸው ውሳኔዎች ተግባራዊ እንዲሆኑ ለስራ አስኪያጁ ትእዛዝ ያስተላልፋል/ታስተላልፋለች::
ረ. የማህበሩን ማኔጅመንት የሥራ አፈፃፀም በቅርብ ይከታተላል / ትከታተላለች፣
ሰ. ጉባኤው ያጸደቀውን የሥራ አፈፃፀምና የአዲት ሪፖርት ለሚመለከታቸው እንዲልክ/እንድትልክ ለስራ አስኪያጁ ትእዛዝ ያስተላልፋል / ታስተላልፋለች፣
ሸ. ከአዲት ሪፖርት ውጭ ያሉትን ዓመታዊ ሪፖርቶች በጉባኤው መደበኛ ስብሰባ ያቀርባል/ታቀርባለች::

4. ምክትል ፕሬዚዳንቱ/ቷ፣

ሀ) ሰብሳቢው በሌለ ጊዜ ሰብሳቢውን ተክቶ/ታ ይሰራል/ትሰራለች፣

3. The president

A. Chairs the meeting of the board
B. Present the decisions of the board to the general assembly
C. Present the association's policies, strategies and directives prepared by the board to the general assembly
D. Depending on the powers vested to the general assembly and the board, is accountable to the assembly and board
E. Orders the manager for implementation of decisions of the board and the general assembly
F. Closely monitors the management performances
G. Orders the manager to sent the performance and audit report approved by the general assembly
H. Present the annual reports except the audit report to the general assembly

4. Deputy president

A. Works in place of the chairman when absent
B. Carries out other activities assigned by the chairman or general assembly

ለ) በሰብሳቢው/ዋ ወይም በጠቅላላ ጉባኤው የሚሰጠውን ተጨማሪ ሥራ ያከናውናል/ታከናዉናለች፡፡

5. ፀሐፊ፣

- ተጠሪነቱ/ቷ ለቦርዱ ነው፣
- የቦርዱን የስብሰባ አጀንዳዎች ከፕሬዚዳንቱ/ዋ ጋር በመነጋገር ያዘጋጃል / ታዘጋጃለች፣
- የቦርዱን ስብሰባ ቃለ ጉባኤ ይይዛል/ትይዛለች፣
- የቦርዱ ጽ/ቤት መዛግብትና ሠነድ ይጠብቃል/ትጠብቃለች፡፡

<u>አንቀጽ 20፡ የሥራ አመራር ቦርድ የስብሰባ፣ የድምጽ አሰጣጥ ሥነ-ስርዓትና የቦርድ አባላት የአገልግሎት ዘመን</u>

1. የቦርዱ መደበኛ ስብሰባ በዓመት ከስምንት - አስራሁለት ጊዜ የሚከናወን ሆኖ አስቸኳይ ስብሰባ የሚያስፈልግበት ምክንያት ሲኖር ልዮ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል፣
2. አስቸኳይ ስብሰባ በቦርዱ ሰብሳቢ ወይም በማህበሩ ሥራ አስኪያጅ ሊጠራ ይችላል
3. ከአባላቱ ውስጥ ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤው እንደተሟላ ይቆጠራል፣ ምልዓተ ጉባኤው ካልተሟላ ድጋሚ ለስብሰባ ጥሪ ይደረጋል፡፡ በድጋሚ በተደረገው ጥሪ ምልዓተ ጉባኤ ካልተሟላ በተገኙ አባላት ስብሰባ ሊካሄድ ይችላል፣
4. ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ይተላለፋሉ፤ ድምጽ እኩል በሚከፈልበት ጊዜ ሰብሳቢው የደገፈው ሃሳብ ይጸናል፣
5. የሥራ አመራር ቦርድ አባል የሥራ ጊዜ አንድ የምርጫ ዘመን (ለሁለት ዓመት) ጊዜ ብቻ ነው፡፡ ሆኖም ለተጨማሪ ሁለት ዓመት በድጋሚ ሊመረጥ ይችላል፡፡

5. Secretary

- accountable to the board
- Prepares the agenda of the meeting of the board by discussing with the chairman
- Records the minutes of the meeting of the board
- Keeps records of board offices and archives

<u>Article 20: The management board meeting, ethics of voting and service years</u>

1. The board meeting shall be eight to twelve times per year and when there is need to emergency meeting, special meeting will be conducted
2. emergency meeting may be called by the board chairman or manager of the association
3. When more than 50% of members are on meeting, the quorum is fulfilled. If quorum is not fulfilled additional meeting will be called. If quorum is not fulfilled on the next meeting will be just conducted.
4. Decisions will be passed by voting; when there are equal votes, the chairman's decision will prevail.
5. The service years of board members shall be two years (one term). However, a board member will not be elected more than two times.

6 የተሰናባቹ የሥራ አመራር ቦርድ አንድ አባል ጊዜውን ከአጠናቀቀ በኋላ ለምርጫ ውድድር መቅረብ ሳያስፈልገው ለቀጣይ አንድ የምርጫ ዘመን አዲስ የተመረጠው የሥራ አመራር ቦርድ አባል ይሆናል፡፡ ይህም ለአዲሱ የሥራ አመራር ቦርድ ልምድ ለማካፈልና ሥራው በቀጣይነት ያለ እንከን እንዲተላለፍ ይረዳል፡፡

7. የቦርድ አባላት ያለደመወዝ ያገለግላሉ፤ ለማህበሩ ስራ ለሚወጡት ወጭዎች ማካከሻ ይከፈላል፡፡

አንቀጽ 21፡ የማህበሩን ሥራ አስኪያጅ ተግባርና ኃላፊነት

የማህበሩ ሥራ አስኪያጅ ተጠሪነቱ ለቦርዱ ሆኖ የሚከተሉትን ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡፡

1. በማናቸውንም አካል ዘንድ ማህበሩን ይወክላል፣ የማህበሩን ስራ በተመለከተ ማናቸውም ጉዳዮች ይፈጽማል፣ ውክልና ይሰጣል፣ በማህበሩ ስም የደብዳቤ ልውውጦችን ያደርጋል፣ ውል ይዋዋላል፡፡
2. በማህበሩ ስም የሚከፈተውን የባንክ ሂሳብ እና ቼክ ወይም ሐዋላ ከሂሳብ ሹሙ ጋር በጣምራ ፊርማ ያንቀሳቅሳል፡፡
3. በጠቅላላው ጉባኤና በቦርዱ የሚተላለፉ ውሳኔዎችን ተግባራዊ ያደርጋል፡፡
4. የማህበሩን የሶስት ወርና ዓመታዊ የሥራና የፋይናንስ ሪፖርቶች እያዘጋጀ (በየሶስት ወሩ እና በየዓመቱ) ለቦርዱ ያቀርባል፡፡
5. የማህበሩን ፖሊሲ በማውጣትና የበጀትና የስራ ዕቅድ በማዘጋጀት ለቦርዱ ያቀርባል፡፡
6. በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት ለማህበሩ ገቢ የሚገኝበትን ዘዴ ይቀይሳል፣
7. ቦርዱ በሚያወጣው የአስተዳደር ደንብ መሰረት ሠራተኞችን ይቀጥራል፣ ያሰናብታል፣ ደመወዛቸውንና አበላቸውን ይወስናል፡፡

6. One of the last members of the leaving board becomes the member of the new board without need for voting.
7. The board members will serve with out salary; but their expenses for the work of the association will be compensated.

Article 21: Duties and powers of the manager

The manager of the association is accountable to the board and has the following duties and powers

1. Represent the association in any place, execute everything of the association, appoint, and exchange of letters on behalf of the association, sign agreements
2. Operate the association bank accounts with common signature of treasurer
3. Implement decisions of the general assembly and board
4. prepares three months and annual performance reports and submit the same to the board
5. set the policy of the association and prepare the budget and activity plans and submit to the board
6. complying with the article of association pave ways of generating revenues and implement strategies to the same
7. in accordance with the regulations of administration assign employees, dismiss, decides their salary and allowances

8. ከሂሳብ ሹምና ከገንዘብ ያዥ የስራ ኃላፊነቶች ውጭ ያሉትን የስራ ድልድሎች በማዘጋጀት ለቦርዱ ያቀርባል፡፡
9. ሂሳብ ሹምና ገንዘብ ያዥን ጨምሮ፣ በስሩ የሚገኙትን ሠራተኞች እያስተባበረ፣ እየተከታተለና እየተቆጣጠረ የማህበሩን የእለት ተዕለት የስራ እንቅስቃሴ ይመራል፡፡
10. የማህበሩን የስራ እንቅስቃሴ በተመለከተ ሌሎች የማኔጅመንት ውሳኔዎችን ይሰጣል፡፡
11. ሥራ አስኪያጁ የማህበሩ አባል ከሆነ ሀሳቡን ለማጽደቅ ወይም በኃላፊነቱ የተከናወነውን ለማጽደቅ በሚደረገው ጠቅላላ ጉባኤ ድምጽ የመስጠት መብት አይኖረውም፡፡
12. የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ ወይም የተቅላላ ጉባኤ ውሳኔን በማቃረን ሁኔታ ከቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

አንቀጽ 22፡ የማህበሩ ሂሳብ ሹም ተግባርና ኃላፊነት

ሂሳብ ሹሙ ተጠሪነቱ ለማህበሩ ስራ አስኪያጅ ሆኖ የሚከተሉት ተግባራና ኃላፊነቶች ይኖሩበታል፤

1. የማህበሩን ገቢና ወጪ ሃሳብ ይቆጣጠራል፣ በትክክል እንዲመዘገብና እንዲያዝ ያደርጋል፡፡
2. የማህበሩ ሂሳብ የሚንቀሳቀሰው በታወቀ የሂሳብ አሰራር ደንብ መሰረት መሆኑን ይቆጣጠራል፡፡
3. የማህበሩን የባንክ ሂሳብ እና ቼክ ወይም ሐዋላ ከስራ አስኪያጁ ጋር በጣምራ ፊርማ ያንቀሳቅሳል፡፡
4. የማህበሩ የሂሳብ መዛግብትና የተለያዩ ሠነዶች በጥንቃቄ እንዲያዙ ያደርጋል፡፡
5. የሂሳብ መዝገብ፣ ገቢና ወጪ፣ ሃብትና ዕዳን ያካተተ ሰነድ ያዘጋጃል፡፡

8. Other than treasurer and accountant, prepares daily job allocations and present to the board
9. Including treasurer and accountant, coordinates the employees, supervises and monitors leading daily activities
10. Regarding operations, renders management decisions
11. If the manager is member of association, has no vote in the approval voting of his idea or responsibility.
12. Carries out other duties from the board complying with articles and decisions of the general assembly.

Article 22: Duties and Responsibilities of the accounts officer

The officer is accountable to the manager and has the following duties and responsibilities

1. Monitoring revenues and expenses of the association, enables correct registry and archive
2. monitors that the accounting system comply with regulations
3. operate the association accounts with common signature of the manager
4. Enabled good archive of accounts of the association
5. Prepares the income and expense, property and debt due

ማህበሩ ገቢ በሚያስገኙ ስራዎች ላይ በሚሰማራበት ጊዜ ለዚሁ ስራ የሚውሉ የተለያዩ የሂሳብ መዛግብት እንዲያዙ ያደርጋል፡፡

አንቀጽ 23፡ የማህበሩ ገንዘብ ያዥ ተግባርና ኃላፊነት

ገንዘብ ያዥ ተጠሪነቱ ለማህበሩ ሥራ አስኪያጅ ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፤

1. የማህበሩን ገቢዎች በህጋዊ ደረሰኝ የሰበሰባል፣
2. የተሰበሰበውን ገንዘብ አገር ውስጥ በሚገኝ ባንክ ገቢ ያደርጋል ገቢ ያደረገበትን ደረሰኝ በጥንቃቄ ያስቀምጣል፣
3. ለሥራ ማስኬጃና ለማህበሩ ጥቃቅን ወጪ ዎች የሚሆን ከብር 2,000.00 (ብር ሁለት ሺህ) ያልበለጠ መጠባበቂያ ገንዘብ ይይዛል፣
4. ከሂሳብ ሹሙ ጋር የወጪ ገቢ ሂሳብ በየወሩ ያመሳክራል
5. የማህበሩን ቼክ ይይዛል፣
6. በጣምራ ፊርማ /በሂሳብ ሹሙና በስራ አስኪያጁ/ ሲታዘዝ ወጪ ያደርጋል፡፡

አንቀጽ 24፡ የኦዲተር ኃላፊነትና ተግባር

1. የማህበሩ ኦዲተር የማህበሩ የስራ አስኪያጅ ወይም የቦርድ አባል ሊሆን አይችልም፡፡
2. ኦዲተሩ ተጠሪነቱ ለጠቅላላው ጉባኤ ሆኖ፤ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

   የማህበሩን የገንዘብና የንብረት አስተዳደር ትክክለኛነት ይቆጣጠራል፣

   የማህበሩ የስራ እንቅስቃሴ በዚህ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት መካሄዱን ያረጋግጣል፣
3. በኢትዮጵያ ተቀባይነት ባገኙ መመዘኛዎች መሰረት ዓመታዊ የኦዲት ሪፖርት አዘጋጅቶ ለጠቅላላ ጉባኤው ያቀርባል፡፡

6. when the association is engaged in revenue generating activities, enables accounting bookkeeping of them

Article 23: Duties and responsibilities of the treasurer

The treasurer is accountable to the manager and has the following duties and responsibilities

1. collect revenues with legal receipt
2. deposit the revenue collected and keeps record of the receipts
3. keeps reserve fund of working capital and activity expenses of up to Birr 10,000 (ten thousand)
4. verify the expense and income accounts with the treasury
5. keeps association's cheque
6. Draw money with common signature of manager and accounts officer

Article 24: Duties and responsibilities of the auditor

1. Auditor cannot be the manager or board member of the association
2. Accountable to the general assembly and has the following duties and responsibilities
   - Monitors the correctness of the money and property of the association
   - Ensures activities of the association comply with the articles
3. In accordance with the regulations of the Ethiopian laws, prepares annual audit reports and present to the general assembly

አንቀጽ 25: የማህበሩ የገቢ ምንጭ

የማህበሩ ዋና የገቢ ምንጭ የአባላት መዋጮ ሲሆን በጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔ ከሕዝባዊ መዋጮ፣ ከገቢ ማስገኛ ስራዎችና ከእርዳታ ሰጪ ዎች የሚገኝ ገንዘብ ወይም ንብረት በገቢ ምንጭነት ሊወሰድ ይችላል።

አንቀጽ 26: የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ ስለማሻሻል

1. የዚህ መተዳደሪያ ደንብ የማሻሻያ ሀሳብ ከጠቅላላ ጉባኤው አባላት 1/4ኛ ባላነሱ አባላት ተያቂነት በስብሰባ አጀንዳነት ይያዛል።
2. የዚህ መተዳደሪያ ደንብ የማሻሻያ ሀሳብ በጠቅላላ ጉባኤ መደበኛ ስብሰባ የሚወሰን ሆኖ የማሻሻያ ጥያቄው ለጠቅላላ ጉባኤው ሰብሳቢ፣ ፀሐፊ ወይም ዳይሬክተር የጉባኤው ጥሪ ከመሰራጨቱ በፊት መቅረብ ይኖርበታል።
3. የመተዳደሪያ ደንብ የሚሻሻለው የማሻሻያ ሃሳቡ ከግማሽ በላይ አባላት በተገኙበት የጠቅላላ ጉባኤው ስብሰባ 3/4ኛ ድምፅ ሲያገኝ ነው።
4. የመተዳደሪያ ደንቡ እዲሻሻል የተላለፈውን ውሳኔ ኤጀንሲው ያላጸደቀው እንደሆን ባልጸደቀበት ጉዳይ ላይ የሚወያይ ስብሰባ ይጠራል።
5. እንዲሻሻል የተወሰነው የመተዳደሪያ ደንብ በኤጀንሲው በኩል ታይቶ ከመጽደቁ በፊት ስራ ላይ ሊውል አይችልም።

አንቀጽ 27: ስለ ማህበሩ መዋሃድና መለመጥ

1. ማህበሩ ወደተለያዩ ማህበራት የሚከፋፈለው ፣ ከሌላ ማህበር ጋር የሚዋሃደው ወይም ወደ በጎ አድራጎት ድርጅትነት የሚለወጠው በጠቅላላ ጉባኤው በ3/4ኛ ድምፅ ሲወሰን ነው።

Article 25: Source of revenue

The major source of revenue of the association is from members' contribution and the local and international donors and up on decision of the general assembly from public contribution, revenue generation activities in cash or in kind.

Article 26: Amending the articles of association

1. the claim for amendment of this article of association by ¼ members will be kept on the agenda of the general assembly
2. the amendment of this article of association shall be by decision of the general assembly and the request for amendment shall be forwarded to chairman, secretary or director before the date of the meeting
3. the amendment of the articles shall be presented to the general assembly of more than half members and voting of ¾ members
4. the meeting will be called for the matter why the agency didn't approve the amendment to the article of association
5. unless the amendment is given consent by the agency, will not be enforced by the association

Article 27: Merging and changing of the association

1. The association will be divided or merged with another associations if the ¾ members of the general assembly give consent to the matter

2. ከማህበሩ ጋር የሚዋሃደው ማህበር ጋር የሚደረገውን ድርድር የሚያከናውነው ኮሚቴ የጠቅላላ ጉባኤውን ፕሬዚዳንት፣ ፀሐፊና የማህበሩን ሥራ አስኪያጅ ማካተት ይኖርበታል።

አንቀጽ 28፡ ስለማህበሩ መፍረስ

1. ማህበሩ የሚፈርሰው የጠቅላላ ጉባኤ አባላት ማህበሩ እንዲፈርስ በ3/4ኛ ድምጽ ሲወሰኑ ነው።
2. ጠቅላላ ጉባኤው ማህበሩን ለማፍረስ ከወሰነበት ቀን አንስቶ ስድስት ወራት ሳያልፍ የማህበሩ ስራ አስኪያጅ የንብረት ዝርዝር (Inventory) አዘጋጅቶ ከማፍረስ ውሳኔው ጋር በማያያዝ ለበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ ያቀርባል።
3. ጠቅላላ ጉባኤው ማህበሩን ለማፍረስ በወሰደው ውሳኔ ላይ የማህበሩን ንብረት ሊረከብ ይገባዋል የሚለውን የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ወይም የመንግሥት አካል ሊያመለክት ይችላል።

አንቀጽ 29፡ የመተዳደሪያ ደንብ የሚጸናበትና ጊዜ

ይህ የመተዳደሪያ ደንብ በበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ከጸደቀበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

2. The merging deal with other associations shall be done where by the chairman; secretary and manager are included in the meeting.

Article 28: Dissolving the association

1. The association will be dissolved up on ¾ decision of the members of the general assembly
2. From the date of decision of the general assembly to dissolve the association, with in six months, the manager shall prepare inventory attached with decision to dissolve and sends the same to the agency of registration of associations.
3. The general assembly can mention the association or welfare or government body to receive the properties after the decision to dissolve the association.

Article 29: Duration of the article of association

This article of association is effective from date of its registration by the Charities and Societies Registration Agency.